የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም መመርያ ቁጥር1082/2017	**Ethiopian Investment Board Directive to Regulate Foreign Investors' Participation in Restricted Export, Import, Wholesale and Retail Trade Investments Number 1082/2025**
የማክሮ-ኢኮኖሚክ፣ የሴክተር እና መዋቅራዊ ሪፎርሞችን በማካሄድ እና ለንግድ እና ኢንቨስትመንት እድገት ተስማሚ ከባቢያዊ ሁኔታን በመፍጠር ፈጣን እና ዘላቂ እድገት ለማስመዝገብ መንግስት የያዘውን ብሄራዊ ትልም ለማሳካት የውጭ ኢንቨስትመንት መስፋፋትን የሚያሳልጡ አዳዲስ አሰራሮችን መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤ ባለፉት አመታት ውስን የንግድ ዘርፎችን ከውጭ ኢንቨስትመንት ውድድር በመከለል የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት፤ ከአለም-አቀፉ የንግድ ትሥሥር ስርአት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ለማስቻል፤ በሂደትም እሴትን ወደሚጨምሩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሸጋገሩ ለማድረግ የሚያስችል ልዩ የንግድ ፖሊሲ ተግባራዊ ሲደረግ ቢቆይም ፖሊሲው አላማውን በሚፈለገው መጠን ማሳካት ባለመቻሉ፤ ከለላ የተሰጣቸው የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የንግድ ዘርፎች ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የጥራት እና የብቃት ችግሮች ሲታይባቸው የቆየ በመሆኑ፤ ክፍተቶችን ለመሙላት የወጣው መመርያ ቁጥር 1001/2016 ለአገር ውስጥ ባለሃብት የተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንት ዘርፎችን በተወሰኑ ቅድመ-ሁኔቶች ላይ በመመስረት ፍላጎትና አቅሙ ላላቸው የውጭ ባለሀብቶች እንዲከፈቱ ቢያደርግም እርምጃው በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ፤	Whereas in order realize the government's national scheme to register rapid and sustainable development by carrying out macroeconomic, sectoral and structural reforms and creating favorable environment for trade and investment, it has been found imperative to put in place new measures that facilitate the expansion of foreign investment; Whereas the special trade policy implemented in the past to protect selected trade sectors from foreign investment competition and thereby facilitate a qualitative and quantitate growth of domestic investors, their integration into the global trade value chain, and eventually their transition to value-added investments - has not attained its objectives on the scale anticipated; Whereas the protected sectors of domestic investments have been subjected to an increasing bent of complaints relating to service reach, quality and efficiency; Recognizing that the measures adopted under Directive No.1001/2024 to fill the gaps by opening the export, import, wholesale and retail trade sectors to willing and capable foreign investors, subject to certain conditions, has been found inadequate; Whereas it is deemed important to re-assess the directive's implementation and carry out new revisions that reinforce investor confidence and facilitate the mobilization of additional foreign capital by creating, as far as practical, procedures that promote equal treatment of foreign and domestic

የመመርያውን አፈፃፀም ዳግም በመፈተሽ እና አዳዲስ ለውጦችን በማከናወን በተቻለ መጠን በዘርፉ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች እኩል የውድድር ሜዳ እንዲያገኙ ማድረግ፣ እንዲሁም የሚቀመጡ የፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎችን ግልፅ፣ ቀላል እና ተገማች በማድረግ የባለሀብቶችን መተማመን ይበልጥ ማሳደግ እና ተጨማሪ የውጭ ካፒታል የሚሳብበትን አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 6(4) እና አንቀጽ 31(1)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመርያ አውጥቷል።	investors and by ensuring that transparent, simplified and predictable procedures are adopted in respect of all permit requirements; Now, therefore, pursuant to its powers vested under Article 6(4) and Article 31(1)(e) of the Investment Proclamation number 1180/2020, the Ethiopian Investment Board has issued this Directive.
ክፍል 1 **ጠቅላላ ድንጋጌዎች**	**PART 1** **General Provisions**
1. <u>አጭር ርዕስ</u> ይህ መመርያ "የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም መመርያ ቁጥር 1082/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።	**1. <u>Short Title</u>** This Directive may be cited as "Ethiopian Investment Board Directive to Regulate Foreign Investors' Participation in Restricted Export, Import, Wholesale and Retail Trade Investments Number 1082/2025''.
2. <u>ትርጓሜ</u> በዚህ መመርያ ፡- 1/ "አዋጅ" ማለት የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው። 2/ "ደንብ" ማለት የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2012 ነው። 3/ "ኮሚሽን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 35 መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው። 4/ "ቦርድ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 30 መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው። 5/ "የውጭ ባለሃብት" በኢንቨስትመንት አዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል።	**1. <u>Definitions</u>** In this Directive, 1/ "Proclamation" means the Investment Proclamation No. 1180/2020. 2/ "Regulation" means the Investment Regulation No. 474/2020. 3/ "Commission" means the Ethiopian Investment Commission re-established under Article 35 of the Proclamation. 4/ "Board" means the Ethiopian Investment Board re-established under Article 30 of the Proclamation. 5/ "Foreign investor'' shall have the meaning accorded to it under the Investment Proclamation. 6/ "Export trade'', "import trade'', "wholesale trade'' and "retail trade'' shall have the meaning accorded to

6/ "የወጪ ንግድ"፣ "የገቢ ንግድ"፣ "የጅምላ ንግድ" እና "የችርቻሮ ንግድ" በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለ) የተሰጠው ትርጉም ይኖራቸዋል። 7/ "የቁም እንስሳ" ማለት የጋማ ከብቶች እና የቀንድ ከብቶች ማለት ነው። 8/ በዚህ መመርያ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቃላት እና ሐረጎች በአዋጁ እና በደንቡ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።	them under the Commercial Registration and Licensing Proclamation No. 980/2008 (as amended). 7/ "Livestock'' means cattle and equines; 8/ Other words and phrases referred to in this Directive shall have the meaning assigned to them under the Proclamation and the Regulation.
3. <u>አላማ</u> የመመርያው አላማ የውጭ ባለሀብቶች ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የሚሳተፉባቸውን መስኮች መዘርዘር እና ተፈፃሚ የሚሆኑ ቅድመ-ሁኔታዎችን በግልፅ መመስረት ነው።	**3. <u>Objective</u>** The objective of this Directive is to list out investment areas in the export, import, wholesale and retail trade sectors hitherto reserved for domestic investors in which foreign investors may now participate and clearly establish the applicable conditions.
4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u> ይህ መመርያ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች በተከለሉ የንግድ ዘርፎች የውጭ ባለሀብቶች በሚኖራቸው ተሳትፎ፣ የፈቃድ ጥያቄ እና ምላሽ አሰጣጥ አሰራር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።	**4. <u>Scope of Application</u>** This Directive shall be applicable on the participation of foreign investors in the trade sectors hitherto reserved for domestic investors, the application of permits, and issuance thereof.
ክፍል 2 **ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በተከለሉ የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንቶች የውጭ ባለሃብቶች ተሳትፎ**	**PART 2** **Participation of Foreign Investors in Export, Import, Wholesale and Retail Trade Investments Restricted for Domestic Investors**
5. <u>በወጪ ንግድ ስለመሳተፍ እና የፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች</u> 1/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ዝቅተኛ ካፒታል፣ ብቃት እና ደረጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በጥሬ ቡና፣ የቅባት እህል፣ ጫት፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳ እና ሌጦ፣ የደን ውጤቶች፣ ዶሮ እና የቁም እንስሳትን	**5. <u>Participation in Export Trade and Permit Conditions</u>** 1/ Without prejudice to the requirements imposed by other laws in relation to minimum capital, competence or standards, any foreign investor can engage in the export trade investment of raw coffee, oilseeds, khat,

ከገበያ በመግዛት የመላክ የወጪ ንግድ ኢንቨስትመንት መሰማራት ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት አንድ የውጭ ባለሀብት በጥሬ ቡና፣ ቅባት እህል፣ ጫት እና ጥራጥሬ ወጪ ንግድ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት በራሱ ወይም በታወቀ አገራዊ ወይም አለማቀፍ አረጋጋጭ ተቋም የተዘጋጀ ዝርዝር የስብእና እና የአቅም መግለጫ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የሚቀርብ ማረጋገጫ ሪፖርት ቢያንስ፣

ሀ) አግባብነት ባላቸው አገር-አቀፍ እና አለማቀፍ የመረጃ ቋቶች እና ሌሎች አሰራሮች ላይ የተቀመጡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ባለሀብቱ በኢትዮጵያ መንግስት ተቀባይነት በሚኖራቸው የማእቀብ ወይም ተመሳሳይ ገደቦች ዝርዝር ውስጥ ያለ መሆን አለመሆኑን የሚያረጋግጥ፣

ለ) በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው አሰራሮችን በመተላለፍ በህገ-ወጥ ተግባራት በተለይም በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ የእፅ ዝውውርን፣ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ማገዝን በተመለከተ አመልካቹ ያለውን ማናቸውም ተመክሮ ምርመራ፣ እና

ሐ) የአመልካቹን የንግድ አሰራር ስብእና እና የፋይናንስ ቁመና ምርመራ ያካተተ መሆን አለበት።

6. በገቢ ንግድ ስለመሳተፍ እና የፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች

1/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ዝቅተኛ ካፒታል፣ ብቃት እና ደረጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከማዳበሪያ እና ነዳጅ ገቢ ንግድ በስተቀር ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በደንቡ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ ሁሉም የገቢ

pulses, hides and skins, forest products, and poultry and livestock bought on the market.

2/ In accordance with sub-article (1) of this Article, any foreign investor shall be permitted to engage in export trade investment of raw coffee, oilseeds, khat, and pulses when it presents a comprehensive due diligence report prepared by itself or a recognized national or international verification agency, detailing the investor's integrity and capacity.

3/ A due diligence verification report submitted in accordance with sub-article (2) of this Article shall at least:

a) screen information availed under the appropriate national or international databases or other procedures to verify whether the investor is not included in any sanctions or comparably restrictive list acceptable by the Government of Ethiopia;

b) evaluate involvement of the investor in illicit activities in contravention of internationally accepted standards, particularly including any experience in money laundering, drug trafficking and terrorism financing; and

c) assess the investor's business integrity and financial standing.

6. Participation in Import Trade and Permit Conditions

1/ Without prejudice to the requirements imposed by other laws in relation to minimum capital, competence or standards, and except for fertilizer and petroleum import trade, any foreign investor can engage in all import trade investments reserved for domestic investors under the Regulation.

2/ Any foreign investor shall be permitted to engage in import trade investment in accordance with sub-article (1) of this Article when it presents a due diligence verification report regarding its integrity and

ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት አንድ የውጭ ባለሀብት በገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት በዚህ መመርያ አንቀፅ 5(2) እና 5(3) ላይ የተመለከተው የስብእና እና የአቅም መግለጫ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

7. በጅምላ ንግድ ስለመሳተፍ እና የፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች

1/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ዝቅተኛ ካፒታል፣ ብቃት እና ደረጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ከማዳበሪያ ጅምላ ንግድ በስተቀር በደንቡ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ ሁሉም የጅምላ ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

2/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት ፈቃድ የሚሰጠው ባለሀብት በአስመጪ ፈቃድ ከውጭ ያመጣው ምርትን ጨምሮ ከአገር ውስጥ አምራቾች የገዛውን ምርት በጅምላ ንግድ መሸጥ ይችላል።

3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1) መሰረት አንድ የውጭ ባለሀብት በጅምላ ንግድ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት በዚህ መመርያ አንቀፅ 5(2) እና 5(3) ላይ የተመለከተው የስብእና፣ የብቃት እና የአቅም መግለጫ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

8. በችርቻሮ ንግድ ስለመሳተፍ እና የፈቃድ ቅድመ-ሁኔታዎች

1/ በዚህ መመርያ መሰረት ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በደንቡ ላይ ለአገር ውስጥ ባለሃብት በተከለሉ የችርቻሮ ንግድ ኢንቨስትመንት መስኮች መሰማራት ይችላል።

2/ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ የብቃት ወይም ተስማሚነት ደረጃዎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (1)

capacity as specified under Article 5(2) and 5(3) of this Directive.

7. Participation in Wholesale Trade and Permit Conditions

1/ Without prejudice to the requirements imposed by other laws in relation to minimum capital, competence or standards, and except for the wholesale of fertilizers, any foreign investor can engage in wholesale trade investment of all sectors reserved for domestic investors under the Regulation.

2/ An investor issued with investment permit pursuant to sub-article (1) of this Article may engage in the wholesale trade of products it imported from abroad using an import trade permit, or products which it acquisitions from domestic producers.

3/ Any foreign investor shall be permitted to engage in wholesale trade investment in accordance with sub-article (1) of this Article when it presents a due diligence verification report regarding its integrity, competence and capacity as specified under Article 5(2) and 5(3) of this Directive.

8. Participation in Retail Trade and Permit Conditions

1/ Pursuant to this Directive, any foreign investor can engage in retail trade investments reserved for domestic investors under the Regulation.

2/ Without prejudice to the requirements imposed by other laws in relation to minimum capital, competence or standards, an investor applying for a permit pursuant to sub-article (1) of this Article shall be issued with investment permit when:

a) the investor raises a paid-up capital of at least USD Two Million Five Hundred Thousand (2,500,000) in cash and assets; and

b) the investor presents a comprehensive due diligence report prepared by a recognized national or international verification agency recommended by the

መሰረት ማመልከቻ የሚያቀርብ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚያገኘው፡ ሀ) ኢንቨስትመንቱ በዓይነት እና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ (2,500,000) የአሜሪካ ዶላር ካፒታል ያለው ከሆነ፡ እና ለ) በኮሚሽኑ በሚለይ የታወቀ አገራዊ ወይም አለማቀፍ አረጋጋጭ ተቋም የተዘጋጀ ዝርዝር የስብእና እና የአቅም መግለጫ ሪፖርት ሲያቀርብ ነው። 3/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) መሰረት የኢንቨስትመንት ድርጅቱ በንብረት የሚመድበው የካፒታሉ ክፍል ግምት ኮሚሽኑ በሚመድበው ባለሙያ የሚረጋገጥ ይሆናል። 4/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (2) የተመለከተው ቢኖርም የውጭ ባለሀብት በአነስተኛ ካፒታል መልካም ስም ባላቸው ነጠላ ምርቶች ችርቻሮ ንግድ የሚሰማራበትን ሁኔታ ቦርዱ በጉዳይ ላይ እየተመሰረተ ውሳኔ ይሰጣል።	Commission, detailing the investor's integrity and capacity. 3/ Any non-cash asset contributed to the paid-up capital of the investment enterprise in accordance with sub-article (2) of this Article shall be valuated by a professional assigned by the Commission. 4/ The stipulation of sub-article (2) of this Article notwithstanding, the Board may issue a decision, on a case-by-case basis, in respect of a foreign investor's participation in reputable single brand retail trade operating on a smaller capital.
ክፍል 3 **የተቋማት የቁጥጥር እና የክትትል ስርአት**	**PART 3** **Institutional Regulation and Monitoring**
9. <u>የተቋማት ሀላፊነት</u> 1/ የሚመለከታቸው አካላት ይህን መመርያ ለማስፈፀም የሚያስችሉ ዝርዝር ተቋማዊ ስርአት ይዘረጋሉ። 2/ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በዚህ መመርያ መሰረት የሚሳለጥ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድን በተመለከተ በገበያ ስርአቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፀረ-ውድድር ተግባራትን ለመቆጣጠር እና የሸማቾችን መብት ለማስከበር የሚያስችል አደረጃጀትና አሠራር ይፈጥራል። 3/ ኮሚሽኑ የውጭ ባለሀብቶችን ማመልከቻ ይቀበላል፤ ተጠባቂ ሁኔታዎች መሟላታቸውን	**9. <u>Responsibilities of Appropriate Bodies</u>** 1/ All appropriate bodies shall establish a comprehensive institutional framework to facilitate the implementation of this Directive. 2/ In respect of wholesale and retail trade activities carried out pursuant to this Directive, the Ministry of Trade and Regional Integration shall establish an organizational structure and procedure to control anti-competition practices that may sway the market system and to protect consumer rights. 3/ The Commission shall receive applications submitted by foreign investors; inspect compliance with required conditions; effect commercial

ይመረምራል፤ አግባብነት ያላቸው ሂደቶችን በመከተል የንግድ ምዝገባ ያከናውናል፤ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፤ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በመሆን አፈፃፀሞችን ይከታተላል።	registration following the appropriate procedures; issue commercial registration certificate and investment permit; and follow through implementations jointly with the Ministry of Trade and Regional Integration.
4/ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኢንቨስትመንት ፈቃድ ላገኙ የውጭ ባለሀብቶች የንግድ ስራ ፈቃድ ይሰጣል፤ የንግድ ስራ ሂደቶችን ይቆጣጠራል።	4/ The Ministry of Trade and Regional Integration shall issue business license to foreign investors who obtained investment permit and shall regulate all trade practices.
5/ በዚህ መመርያ ማእቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ስራዎች የተፈለገውን አላማ እያሳኩ መሆኑን ለመመዘን እና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች በቦርዱ የሚሰየሙ አካላት አንድ ቋሚ የጋራ ኮሚቴ ያደራጃሉ። አፈፃፀሙን ይከታተላሉ። የቋሚ የጋራ ኮሚቴው ሰብሳቢ በቦርዱ ይሰየማል።	5/ The Ethiopian Investment Commission, the Ministry of Trade and Regional Integration, the Ministry of Industry, the Ministry of Revenue, the Ministry of Agriculture, Customs Commission, the National Bank of Ethiopia and other bodies designated by the Board shall establish a permanent joint committee to assess whether the activities implemented under this Directive are achieving the desired objectives, to adopt timely actions, as necessary, and monitor the overall implementation. The Chair of the Joint Committee shall be designated by the Board.
ክፍል 4 **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**	**PART 4** **Miscellaneous Provisions**
10. <u>የመተግበር ግዴታ</u> 1/ በዚህ መመርያ የተሸፈኑ ጉዳይ የሚመለከተው ማንኛውም የፌዴራል መንግሥት አካል መመርያውን የማክበር እና የመፈጸም ግዴታ አለበት። 2/ ማንኛውም ሰው ወይም አካል ለዚህ መመርያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።	**10. <u>Duty to Implement</u>** 1/ Any federal government body having mandate in respect of matters covered in this Directive shall have a duty to respect and execute the Directive. 2/ Any person or entity shall have the obligation to cooperate in the implementation of this Directive.
11. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u> 1/ 'የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በተከለሉ የወጪ፣ ገቢ፣ ጅምላ እና ችርቻሮ ንግድ ስራዎች የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት ተሳትፎ አፈፃፀም መመርያ ቁጥር 1001/2016' ተሽሯል።	**11. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>** 1/ The 'Ethiopian Investment Board Directive to Regulate Foreign Investors' Participation in Restricted Export, Import, Wholesale and Retail Trade Investments No.1001/2024' is hereby repealed.

2/ ይህን መመርያ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሠራር በዚህ መመርያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።	2/ No law or practice shall have effect with respect to matters provided for in this Directive so far as it is inconsistent with this Directive.
12. <u>መመርያው የሚጸናበት ጊዜ</u> ይህ መመርያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በኮሚሽኑ ድህረ-ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።	**12. <u>Effective Date</u>** This Directive shall come into force as of the date on which its registration with the Ministry of Justice and its uploading on the official website of the Commission.
አምባሳደር ግርማ ብሩ **የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ሰብሳቢ**	**Ambassador Girma Birru** **Chair: Ethiopian Investment Board**